# ቲ.ፒ.ሌ.ኤፍ የእብዶች ማህበር

*ሥረጉተ ሥላሴ*
*ሰኔ 2001 ዓ.ም.*

ህሊና ሲስት፤ ህሊና ሲሰወር፤ ህሊና ሲታወር፤ ህሊና ሲዛቅጥ፤ ህሊና ሲክድ እብድነት ያመጣል። የትግሬው ነፃ አውጪው ድርጅት ህመምተኛ ነው። የሚሰራውን ብቻ ሳይሆን የቆመበትን መሬት እንኳን መለዬት የተሳነው ጉድ።

በዕውነት ነፃ አውጪው መጀመሪያ ነፃ ማውጣት ያለበት እራሱን ይመስለኛል። በሀቅ፤ በዕውነታ ጠበል መጠመቅ። በታሪክ እንደዚህ ዘመን የታመሰ ዘመን ከቶ አልታዬም። የበደሉ ክርፋት መጠንም ልክም ማውጣት የሚቻል አይደለም።

እርሀቡ፣ በሽታው፣ አፈናው፣ ግድያው፣ ስደቱ፣ እሰራቱ፣ ሀገር መመዝበሩ፣ መሸጥ መለወጡ፣ ሁለመናው የመገለ የገለማ። ልኩ የአለፈ ረመጥ! የሆመጠጠ የምጥ ጊዜ። ይህንን ነው እና አቦይ ስብሀት ደረታቸውን ነፍተው ትክክል ሠርተናል የሚሉት።

ለመሆኑ ከእብዶች ማህበር መሪዎች ላይ ዓይን የሚሉት የአካል ክፍል ማዬት ይቻል ይሆን? እርግጥ ህሊናን ማዬት ይቸግራል። ለነገሩ ጠንጋረው ድረጊታቸው እራሱ የህሊናቸውን ዕወርነት ያውጃል።

አንድ የበከተ ድረጊት፤ በበደል የበሸቀጠ የጎሳ ድርጅት፤ በክፋት የተላ ጎጠኛ ድርጅት፤ በግፍ የደለበ የመንድር ስብስብ ሀገርን እየገደለ ድኅነትን አምጥተናል ማለት ከእበድነት ሌላ ከቶ ምን ሊባል ይችል ይሆን?

በሁሉም መስክ በቁመናችን እያረገፈን፤ እየሸጠን እየለወጠን፤ እየገፋ እየገደለ፤ ድሆኖ ገልብጥ የአራዊት ስብስብ  በልበ ሙሉነተ መለካም አድርገናል ማለት በሽተኝነት ነው። አእምሮን የሳተ ረግረጋማዊ ግልብጥ ተረት ተረት ነው።

ትውልዱን እኮ አንጠላጠሉት ... አብጠለጠሉት፡ በታሪኳ ቅኝ ተግዝታ የማታውቀው ወርቅ ሀራችንን እሱም ቆረቆራቸው እና መሬቷን ለውጭ ኃይሎች በመቸብቸብ ቅኝ ተገዢ ለማድረግ መንደፋደፍ ... ግን ምን ይባሉ እነኝህ ጉድጓዶች!

መርዛቸው እኮ የአልነካው፡ የአላሸተተው ያልደረሰበት መስክ ከቶውንም የለም። ጉዑዙ ነገር እራሱ አፍ አውጥተህ ተናገር ቢባል በዕንባ የሚገልፀው **የገማ ግፍ አሸኮኮ አድርጎ እየተገፋ፤ እየተገፈተረ መቀመጡን ይገልጣል።** አይደለም ሰዋዊው ፍጡር። ግን እሰከ መቼ? ዳር ቁመን ወይንስ  ... ? ጊዜውን እናሻማ! ሳይመሽብን! እንቅደመው! እንሩጥ!

ደግሞ እንዲህ ሳያፍሩ አንገታቸውን ሳይሸማቀቅ በህዝብ መገናኛ እነ አቦይ ስብሃት ያጓሩብናል። በዛ በጣም በዛ። ዛሬ በህግ እያስተዳደርነው የሚሉት ጨዋው የኢትዮጵያ ህዝብ በአህቲ ልቦና ሆ! ብሎ የተነሳ ማዕልት ወዮ ነው ወዮ! ያኔ የአጋዚ አራዊት አጋሰሶች በራሱ በአናቱ ይዘቀዘቃል።

የህዝብን የቆረጠ! የወሰነ! ሞገድ የሚያግደው ምንም እና ማንም ኃይል አይኖርም! ድገሞም አይቀርምምም!

በደሉ ሞልቶ ተረፈ ከልክ በላይ ፈሰሰ! ለአንድ ቀን ሴኸ ሆኖ ተቀምጧል። በሰፈሯት ቁና ...

**ዕልፍ ነን እና ዕለፍነታችን እልፍ እናድርገው!**
**ትውልዳዊ ድርሻችን በህብረት እና በቆራጥነት እንወጣ!**